# የኢትዮጵያ ቀጣዩን ጠቅላይ ሚኒስተር ማን ይሁን?

በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ቀጣዩን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር ተመርጦ ይፋ የሚሆንበት ግዜ በጣም ቅርብ ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ሃ/ማርያም ደሳለኝ ከመንግስትና ከድርጅት የሥራ ሐላፍነታቸው እንዲለቁ ከጠየቁበት ግዜ አንስቶ ስለቀጣዩን ጠቅላይ ሚኒስተር ማን ይሁን? እያሉ የተለያዩ ወገኖች ከተለያዩ ምክንያቶች በመነሳት የየራሳቸውን መልስ ሲያስቀምጡ ሥያስደምጡን ሥነባብቷል፡ ተደምጠዋል። እነዚህ ወገኖች ምክንያታውነት ያላቸው እና ከምክንያታውነት በጣም የራቁም ናቸው።

አንድ አንዶዎቹ ጠባብ ብሔርተኝነት መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ ሌሎቹን ደግሞ ከተራ ስሜታውነትና አላዋቂነት ፍላጎታቸውን ሊያጋሩን ሲሞክሩ ቆይቷል። ከመልካም ኢትዮጵያዊነት በመነጨ እና አገራዊነትም ከተላበሰ መንፈስ እንትና ቢሆን እያሉ ሐሳባቸውን ሲያስደምጡን የቆዩም በርካታ ናቸው። በነገራችን ላይ ትምክሕተኛም ጠባብተኝነት አለው ጠብብተኝነት ያለው ትምክሕተኝነት ሊያስተናግድ አይችልም እንጂ።

ሁሉም ስለአገሩ ያገባዋል የመሰለው መተንበይ እና መመኘት ያለ ገደብ ሊከበርለት የሚገባ መብትን ነው። ኢትዮጳውያን በታሪካችን ሊመራን የሚገባ እንትና ይሁን ለማለት ስለበቃን ኢህአዴግ ምስጋና ይድረሰው እሰየ ነው። ኢህአዴግ ካስገኘልን አንዱ ቱርፋት ስለመሪዎቻችን ስለመንግስትም ለመናገር መብቃታችን ነው።

ቀጣዩን ጠቅላይ ሚኒስተር እንትና ይሁን ለማለት ግን መመዘኛችን ምን መሆን አለበት? በጥንቃቄ ማየትና መመርመርን በጣም ተገቢና ለአገሪቱ በጣም ተፈላጊ ነው። በእኔ እይታ መመዘኛዎቹን ምን መሆን ይገባቸዋል? ብየ እንደሚቀጥለው ለመመለስ ከውስጤ ስመክር ቆይቻሎህ። መመዘኛዎቹም

1) የድርጅቶዎቹ በየክልላቸው ያስገኙት የሥራ ውጤት።
2) የድርጅቶዎቹን የሊቀ-መናብርት የሥራ ልምድና የአመራር ብቃት።
3) ለሚፈጠሩ ወይም አሁን ላይ ላሉ ችግሮች የመፍታት አቅማቸው።
4) አገራዊ ሐላፊነትን ለመወጣት ያላቸውን ዝግጁነት።

የመሳሰሉት በሚገባ በመርመር እንትና ጠ/ሚኒስተር ቢሆን ተመራጭ ነው ብለን ለመተንበይ ልንበቃ ይገባል። እንኳን እኛ ኢህአዴግም እነዚህን መሰረት በማድረግ ሊቀመንበሩን መምረጥ እንዳለበት ነው የሚሰማኝ። ከላይ ያሉት መመዘኛዎች በመውሰድ የበኩሌን አስተያየት እንደሚቀጥለው ይሆናል። አንድ በአንድ ድርጅቶቹን እና የክልል መንግስታትን ለያይቸ በመተንተን ቀጣዩን ጠ/ሚኒስተር ማን ይሁን መልሴን ላካፍላቹህ።

የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንደ ድርጅት መገምገም ያለብን በየክልላቸው የሚመሩት መንግስት ቁመናን በመፈተሽ ለምንፈልገው መልስ መድረሻ ግንዛቤ እንድናገኝ ይረዳል። በፌደራል ያሉትም መፈተሽ ቢገባም ብንችልም ትክክለኛው የየድርጅቶች መልክ እና ቁመና ግን ያለው በየክልላቸው ነው። የፌደራሉ በተለያዩ ስብስቦች የሚተገበር የጋራ ሥራዎች ስለሆኑ አንዱን ድርጅት ለይተህ ለመፈተሽ እንደ አማራጭ አልወስድም። ለእኔ ቀላሉ እና ወሳኙ መመዘኛ ድርጅቶቹን ለይተህ የምታይበት ክልሎቹን ሆነው ነው የታዩኝ። በዚህ የእኔ የመፈተሻ አካሔድ አብረን ብንፈትሽ እንደሚቀጥለው እናገኘዋለን።

# ህ.ወ.ሓ.ት.

እንደ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በክልሉ መልካም አስተዳደርን ፍትሐውነትን ዴሞክራስያውነትን የሚፈለገውን ያህል ያላረጋገጠ። ክራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን በሚፈለገውን ያህሉን ያላዳከመ። የትግራይ ህዝብ የታገለውንና የከፈለውን መስዋእት የሚመጥን የትግል ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለ ድርጅት ነው።

ባለፉት ጥቂት ወራት ህወሓት ውስጡን መርምሮ ችግሮቹን ለይቶ ተግቢ እርምት ወስዶ ለትግበራው በመንገድ ላይ ያለ ድርጅት ነው። የአመራሮች ለውጥ አድርጎ በአዲስ አመራር ሐላፍነቱን ለመወጣት ለትግል የተዘጋጀበት ሁኔታ እንዳለ ነግሮናል። ውጤቱን ግዜው ጠብቆ የምናየው ይሆናል።

ድርጅቱ ከላይ ያሉ የክልሉ ችግሮች ቢኖሩም ግን በክልሉ ህዝቡን በሰላማዊ መንገድ እንዲጠይቅና እና እንዲታገል ያስቻለ አማራር ሢሰጥ ቆይቷል። የቀድሞው አማራርና የአሁኑ አመራር ይህንን በሚገባ መፈፀም ችለዋል።

ህወሓት ኢህአዴግ በአመራሩ ውስጥ ተገቢውን ትግል ያደረገና እስከ ታች ወርዶ ድርጅቱን አደጋ ውስጥ ሊከት ከሚችለው አደጋ ካለ ምሕረት የታገለ ከኢህአዴግ ቀዳሚ ድርጅት ነው። መቻቻልን ያስወገደ ትግል አካይደዋል። ስለዚህ በአራቱ መመዘኛዎች ህወሓት ሲገመገም

1) የድርጅቶዎቹ በየክልላቸው ያስገኙት የሥራ ውጤት። እንደ ሁሉም ድርጅቶች ተመሳሳይ ቢሆንም ግን በክልሉ ህዝቡን በሰላማዊ መንገድ እንዲጠይቅና እና እንዲታገል ያስቻለ አማራር ሢሰጥ ቆይቷል። የቀድሞው አማራርና የአሁኑ አመራር ይህንን በሚገባ መፈፀም ችለዋል። በክልሉ ሰላም በማስጠበቅ በኩል ሥራው በተገቢ ሰርተዋል።
2) ለሚፈጠሩ ወይም አሁን ላይ ላሉ ችግሮች የመፍታት አቅማቸው። ዶ/ር ደብረፅየን ችግር ከመፍታት አንጻር ብቁ ሰው ነው። የድርጅት የውስጥ ችግር መፍታት እና መታገል ነው ከባዱ ነገር ይህንን በተገቢ ያስቻለ ሰው ነው።
3) አገራዊ ሐላፊነትን ለመወጣት ያላቸውን ዝግጁነት። ዶ/ር ደብረፅዮን አገራዊ ሐላፍነትን ለመውሰድ ብቃት ያለው ሰው መሆኑን በሚኒስተርነት በነበረበት ግዜ አስመስክረዋል። ብቁ ሰው ነው።
4) የድርጅቶዎቹን የሊቀ-መናብርት የሥራ ልምድና የአመራር ብቃት። ዶ/ር ደብረፅየን ገ/ሚካኤል የአጪር ግዜ የድርጅት የአማራር ልምድ ነው ያለው። ገና ልምዱ ያልተፈተነ ነው። ህወሓትን ከአደጋ በመታደግ በኩል ጠንካራ ሰው ነበር። ኢህአዴግንና ኢትዮጵያን ከመታደግ አንጻር ጠንካራ ሰው መሆኑን አስመስክረዋል። የኢህአዴግ ሊቀመንበር ለመሆን ግን ገና በሥራ መፈተን ያስፈልገዋል። ለምክትል ሊቀመንበርነት ህወሓት ዶ/ር ደብረፅየንን ብያቀርብ ግን ተገቢ ይመስለኛል።

ሌላው ዶ/ር ደብረፅየን ሁለት የሚኒስትርነት ዘመን በሐላፊነት ላይ ስለ ነበር ለጠ/ሚኒስተርነት ቢመረጥ እንኳን እስከ የሚቀጥለው የምርጫ ዘመን ማለት ከሚቀጥሉት ሁለት አመታት የሚዘል የጠ/ሚኒስተርነት ግዜ የበለጠ አይኖረውም። ለዚህ ተብሎ ደግሞ ህወሓት ዶ/ር ደብረፅየን ጠ/ሚኒስተር ለመሆን የሕግ ድጋፍ ስለማይኖረው የጠ/ሚኒስቲርነት ቦታ ለመያዝ ብሎ ሌላ የህወሓት መሪ መምረጥ አይጠበቅበትም። ለስልጣን ሽኩቻ ካልፈለገ በቀር።

ስለዚህ ህወሓት ለጠ/ሚኒስተርነት ባያቀርብ ይመረጣል። ቢያቀርብ ግን እንደ እኔ ሌላ የተሻለ ሰው ስላለ ከህወሓት ጠ/ሚኒስተር ባይመረጥ ይሻላል እላሎህ።

# ብ.አ.ዴ.ን.

ብአዴን እንደ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በክልሉ መልካም አስተዳደርን ፍትሐውነትን ዴሞክራስያውነትን የሚፈለገውን ያህል ያላረጋገጠ። ክራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን በሚፈለገውን ያላዳከመ። የአማራን ህዝብ የታገለውንና የከፈለውን መስዋእት የሚመጥን የትግል ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለ ድርጅት ነው።

ብአዴን በክልሉ ሰላም ማስፈን ያልቻለ ድርጅት ነው። ዘር ተኮር ጥቃቶች በተደጋጋሚ የሚተናገድበት ክልል ነው። የሌሎች ኢትዮጵያውያን መብት ያላስጠበቀና ያልታደገ የክልል መንግስትና ደርጅት ነው። (በቅማንት እና በአማራ መካከል የተፈጠርው ግጭት፡ በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰው ጥቃት መገለጫዎቹ ናቸው)

ብአዴን ኢህአዴግ ባስቀመጠው የግምገማ አቅጣጫ ውስጡን ለመፈተሽ የተሳነው ድርጅት እና መቻቻልን ያላሰወገደ ድርጅት ሆኖ ነው የቀረው። ውስጠ ትግሉን የተዳከመ እርስ በእርሱ የተፈራራ ድርጅት ነው። በክልሉ ላሉ ችግሮች ተጠያቂዎች መለየት ያልቻለ ድርጅት ነው።

ባለፈው ኢህአዴግ እስሮኞች ለመፍታት ባስቀመጠው አቅጣጫ መፈታት ያለባቸው እስሮኞች በሰው ሂወት አደጋ ያላደረሱ ወይም እንዲደርስ ያላነሳሱ ያልመሩ። በንብረት አደጋ ያላደረሱ ወይም እንዲደርስ ያላነሳሱ ያልመሩ የሚል መመርያ አስቀምጦ ነበር። ብአዴን ግን ከተቀመጠው አቅጣጫ ወጥቶ በ11 የፌደራል ፖሊስና በመከላከያ ሰራዊት አባል ግድያ የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም ምክንያት የነበረውን የቀድሞ ኮለኔል ነበር እንዲፈታ ምሕረት አድርገዋል። ስለዚህ ብአዴን እንደድርጅት ሐላፍነቱን ከመወጣት አንጻር ሲታይ ብልሽት ሚዛኑን የደፋበት ወይም ከመስመሩ ፈቀቅ እያለ ያለ ይመስላል።

እና ከብአዴን ጠ/ሚኒስተር ሊመጣ ይገባልን? መስፈርቶችን መሰረት አድርገን እስቲ ብአዴን እንመርምር?

1) የድርጅቶዎቹ በየክልላቸው ያስገኙት የሥራ ውጤት ቢፈተሽ ብአዴን የክልሉን ሰላም ማስጠበቅ ያልቻለ ደርጅት ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ወይም ከዛ በፊት ጀምሮ እስካሁን የቀጠሉ በክልሉ የሰላም መታወክ ማስተካከል ያልቻለ የክልሉ መንግስት ሆነዋል።
2) የድርጅቶዎቹን የሊቀ-መናብርት የሥራ ልምድና የአመራር ብቃት። ብአዴን እንደ ድርጅት የሚመራ ብቃት የሌለው አመራር መሆኑን ከላይ የተገለጹትን ያሳዩናል።
3) ለሚፈጠሩ ወይም አሁን ላይ ላሉ ችግሮች የመፍታት አቅማቸው። በክልሉ ለተፈጠሩ ሁከትና መበጣበጥ መፍታት ያልቻለው ድርጅት ሆኖ ተገኝተዷል ብአዴን። ስለዚህ አገርን ለመምራት የሚያስችል ቆመና የሌለው ድርጅት ነው ለማለት የሚያስደፍር ድርጅት ነው።
4) አገራዊ ሐላፊነትን ለመወጣት ያላቸውን ዝግጁነት። ክልላዊ እና ድርጅታዊ ሐላፍነትን ያልተወጣ ብአዴን አገራዊ ሐላፍነትን ይወጣል ብሎ ለማመን በእውነት በጣም አስቸጋሪ ነው።

ስለዚ ብአዴን ለኢህአዴግ ሊቀመንበርነት ይቅር ለምክትል ሊቀመንበርነትም ሰው ማቅረብ የሚያስችል ህሊናዊ ዝግጁነት ሊኖረው አይገባም። ለኢህዴግ ሊቀመንበርነት ሰው ከሚያቀርብ ይልቅ ብአዴን በድጋሜ ውስጡን መፈተሽ እና መቻቻልን ተሻግሮ ድርጅቱን ካለበት የመስመጥ አደጋ ቢታደግ ተገቢ ይመስለኛል።

# ኦ.ህ.ዴ.ድ.

ኦህዴድ እንደ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በክልሉ መልካም አስተዳደርን ፍትሐውነትን ዴሞክራስያውነትን የሚፈለገውን ያህል ያላረጋገጠ። ክራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን በሚፈለገውን ያላዳከመ። የኦሮሞ ህዝብ የታገለውን ያህል የሚመጥን የትግል ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለ ድርጅት ነው።

ኦህዴድ በክልሉ ሰላም ማስፈን ያልቻለ ድርጅት ነው። ዘር ተኮር ጥቃቶች በተደጋጋሚ የሚስተናገድበት ክልል ነው። የሌሎች ኢትዮጵያውያን መብት ያላስጠበቀና ያልታደገ የክልል መንግስትና ደርጅት ነው።

ኦህዴድ ውስጥ የገረሙኝ ሁለት ነገሮች አሉ። የኢህአዴግ እህት ድርጅቶች አራቱ ሊቀመናብርት አንድ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ግዜ አቶ ለማ መገርሳ ሁለት ያስገረሙኝ ነገሮች ተናግረው ነበር።

አንደኛ ህወሓት ላይ የተፈጠረው ቡድናዊ መከፋፈል ኦህዴድን ችግር ውስጥ እንድንገባ እና እንድንከፋፈል አድርጎናል። ብለውን ነበር። በጣም ይገርማል ኦህዴድ ጤናማ ከሆነ እንዴት ነው የህወሓት መበላሸት ኦህዴድን ሊያበላሽ የሚችለው? የአቶ

ለማ አባባል የሚያመላክተው ኦህዴድ ውስጡን ለመፈተሽና ውስጠ ትግል ለማድረግ ዝግጁነት እንደሌለው ነው ያሳዩን። የኦህዴድ ችግር ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ከእውነተኛ ታጋይ እና መሪ የሚጠበቅ አይደለም። ኦህዴድ ባካሔደው ግምገማ ግን አቶ ለማ ካሉት በተለየ መልኩ የተፈጸመ ይመስለኛል። ኦህዴድ ውስጡን ለመፈተሽ የፈተነ ይመስለኛል።

ሁለተኛው በዛን ግዜ አቶ ለማ ያሉት ለህዝብ የማይሆን ስልጣን ገደል ይግባ ብለውን ነበር። በተግባር ግን አላሳዩንም። ከንግግራቸው በኋላ ኦሮምያ ክልል ሁከትና ረብሻ ተፈጥረዋል። የክልሉ ህዝብ ሰላሙን አጥተዋል። ይህንን ደግሞ የአመራር ውጤት ነው። ስለዚ አቶ ለማ ክልሉን በብቃት መምራት አልቻሉም። ኦህዴድን በሚገባ መምራትም አልቻሉም። ታድያ እስከአሁን በስልጣን ላይ ምን ያደርጋሉ?

ኦህዴድ በአሁኑ ሰዓት ለኢህአዴግ ሊቀ-መንበርነት የሚበቃ ሰው ማቅረብ ይችላልን? እስቲ ኦህዴድን እንፈትሸው?

1) የድርጅቶዎቹ በየክልላቸው ያስገኙት የሥራ ውጤት አስመልክተን ኦህዴድን ብንገመግመው ኦህዴድ በሚመራው ክልል የህዝቡን ሰላም ማስጠበቅ ያልቻለ ድርጅት ነው።
2) የድርጅቶዎቹን የሊቀ-መናብርት የሥራ ልምድና የአመራር ብቃት። ዶ/ር አብይ አህመድ በቅርቡ የተመረጡ በመሆናቸው የአመራር እና የስራ ብቃታቸው ገና ያልተፈተኑ ናቸው። ብቁ ናቸው አይደሉም ለማለት ባይቻልም በኦሮምያ ክልል ያለውን አለመረጋጋት ግን ጥርጣሬ ውስጥ ሊጥላቸው ይችላል።
3) ለሚፈጠሩ ወይም አሁን ላይ ላሉ ችግሮች የመፍታት አቅማቸው። ክልላዊ ችግሮችን መፍታት ያልቻለና መፍታት የሚችል አመራር መፍጠር የተሳነው ድርጅት አገራዊ ችግርን ይፈታል ብሎ መተንበይ በጣም ያዳግታል። ከሌሎች ክልሎች ለተፈጠረው ግጭት ኦህዴድ መፍታት የተሳነው እና ፌደራል እንዲገባ ምክንያት የሆነ ድርጅት ነው ኦህዴድ። ስለዚ አገራዊ ችግር ቢከሰት በመሪነት መፍትሔ ማምጣት የማይችል ይሆናል።
4) አገራዊ ሐላፊነትን ለመወጣት ያላቸውን ዝግጁነት። ክልላዊ ሐላፍነትን መወጣት ያልቻለ አመራር እና ድርጅት አገራዊ ሐላፍነትን ለመወጣት ዝግጁነት አለው ከማለት ይልቅ ዝግጁነቱ ያንሰዋል ማለት ይቀላል።

ስለዚህ ኦህዴድ ለኢህአዴግ ሊቀመንበርነት ሰው ማቅረብ ድፍረቱ ሊኖረው አይችልም አይገባምም። ከብአዴን ጋራ ቢወዳደር ግን ብያንስ ውስጡን የፈተሸ እና መቻቻልን በተወሰነ ርቀት ያስወገደ በመሆኑ ለምክትል ሊቀመንበርነት ቢያቀርብ ከብአዴን በልጦ ሊታይ ይችላል።

# ደ.ኢ.ህ.ዴ.ን.

ደኢህዴን እንደ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በክልሉ መልካም አስተዳደርን ፍትሐውነትን ዴሞክራስያውነትን የሚፈለገውን ያህል ያላረጋገጠ። ክራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን በሚፈለገውን ያላዳከመ። የኦሮሞ ህዝብ የታገለውን ያህል የሚመጥን የትግል ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለ ድርጅት ነው።

ሦስቱን የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች፡ ማለት ህወሓት፡ ብአዴን፡ ኦህዴድ፡ ለጠ/ሚኒስተርነት እንደ እኔ እምነት ማቅረብ ወይ መወዳደር የለባቸውም ካልኩኝ፡ ብቸኛው ለጠ/ሚኒስተርነት ብቃት ያለው ሰው ማቅረብ ያለበት ደኢህዴን ብቻ ነው ማለት ነው። ለምን እንዲህ አይነት እምነት ለመያዝ በቃሁኝ? ምክንያቶቼን እንደሚቀጥለው ላቅርብ። አራቱን መመዘኛ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ እንየው።

1) የድርጅቶዎቹ በየክልላቸው ያስገኙት የሥራ ውጤት። ደኢህዴን እንደ ድርጅት ክልሉን ከብአዴንና ኦህዴድ በተሻለ በሰላማዊ መንገድ መምራት የቻለ እና አንድ አንድ ሰላም የሚያውኩ ሁኔታውን ቢፈጠሩ እንኳን የተከሰቱትን ችግሮች ለመፍታት ሐላፊነቱን በብቃት መወጣት የቻለባቸው ስራዎችን ለማየት አብቅቶናል። ስለዚህ ድርጅቱ ክልሉን አልፎ አገርን የመምራት ዝግጁነት እንዳለው በተግባር አስመስክረዋል።
2) የድርጅቶዎቹን የሊቀ-መናብርት የሥራ ልምድና የአመራር ብቃት። የአቶ ሽፈራው ሽጉጤ የአመራር ብቃት የደቡብ ክልል ሊቀመንበር በነበረበት ግዜ ስራውን እና ሐላፊነቱን በአግባብ በህዝብ የተሰጠውን ሐላፊነትን መወጣት የቻለ

*መሪ መሆኑን አይተናል። መንግስት የመምራት ልምዱ ከሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሊቀ-መናብርት ጎልቶ ለመታየት በቅተዋል። በስራ ተፈትነዋል። ዶ/ር አቢይ አህመድ እና ዶ/ር ደብረፅየን በመንግስት እና በድርጅት አመራርነት ገና ተፈትነው ያላለፉ ሲሆኑ፡ አቶ ደመቀ መኮነንን ግን ብአዴንን በመምራት ፈተናው የወደቁ ሰው ናቸው።*

3) *ለሚፈጠሩ ወይም አሁን ላይ ላሉ ችግሮች የመፍታት አቅማቸው። አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ችግር የመፍታት አቅማቸው ከላይ እንደገለጽኩት አመስክረዋል።*
4) *አገራዊ ሐላፊነትን ለመወጣት ያላቸውን ዝግጁነት። አቶ ሽፈራው ሽጉጤ አገራዊ ሐላፍነት ለመወጣት ዝግጁነታቸው ከስራ ልምዳቸው መመልከት እንደሚቻለው ብቁ ናቸው ለማለት ድፍረቱ አለኝ።*

*ስለዚህ ኢህአዴግ ለሊቀመንበርነት በአሁኑ ወቅት የተገኙት ብቸኛ ሰው አቶ ሽፈራው ሽጉጤን ናቸው ለማለት ምንም አጠራጣሪ ነገር የለውም።*

*አንድ አንድ ግዜ የሚሰሙ አቶ ለማ መገርሳ፡ አቶ ስራጅ ፈጌሳ፡ ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገ/ዝግአብሔርን ጠ/ሚኒስተር ቢሆኑ የሚሉ ትንበያዎች አሉ። እነዚህ አባባሎች ከምን መስፈርት ወደ እንደዚህ ትንበያ መድረስ እንደተቻለ ምክንያታዊ ትንተናዎች የሉም። ይህንን አይነት ፍላጎት ያላቸው ወገኖች ግን የግንዛቤ ማነስ ያለባቸው ወገኖች ሳይሆኑ አይቀሩም። ምክንያታዊ ያልሆንበትን ነገር ምንድነው? ማየቱን ተገቢ ይመስለኛል። የአገሪቱን ጠ/ሚኒስተር የሚሆነው የኢህአዴግ ሊቀመንበር ነው። የኢህአዴግ ሊቀመንበር መሆን ያለበት ደግሞ ከአራቱ የድርጅቶች ሊቀ-መናብር አንዱ ነው። የኢህአዴግ እህት ድርጅቶች ምክትል ሊቀ-መናብርት የኢህአዴግ ሊቀመበር እና ጠ/ሚኒስተር የሚሆንበት ምንም አይነት ህጋዊ ድጋፍ አይኖረው። የመጣበትን ድርጅት ሊቀ-መንበር ለመሆን ያልበቃ ሰው የኢህአዴግ ሊቀ-መንበርስ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ለትንበያ ይቀርባል? አንድ ነገር ከማለት በፊት የምትለውንና የምታስበውን ለመድረስ ነገሮችን ትክክለኛ ምንነታቸውን ማወቅ ቀዳሚ መሆን ተገቢ ነው።*

*ሌላው ስለ ቀጣዩ ጠ/ሚኒስተር ማን ይሁን? ብለው አንድ አንድ ወገኖች ሲመልሱ ከኦሮሞ ቢሆን ይሻላል። አይደለም ከአማራ ቢሆን ይሻላል የሚሉ አሉ። ይህንን የሚጋሩ ወገኖች ከሁለት ምክንያቶች ይተነትናሉ።*

*ሀ) ከትግራይ እና ከደቡብ ላለፉት አመታት ኢትዮጵያን ስለመሩ አሁን ተራው ከኦሮሞ ወይም ከአማራ መሆን አለበት ይሉናል።*

*ለ) የኦሮሞ ህዝብ ከሌሎች ብሔር ብሔረ-ሰብ ብዛት ያለበት ህዝብ ስለሆነ ከኦሮሞ መሆን አለበት። አማራም ብዙ ህዝብ ስለሆነ ከኦሮሞ ካልሆነ ከአማራ መሆን አለበት የሚሉም አሉ።*

*አንደኛ የመንግስት ስልጣን እንደ ጠበል ሁሉም ይቅመሰው የማለት አስተሳሰብ በእውነት በጣም ያሳዝናል። ይህንን የእኩልነት መገለጫ አድርገው ያሰቡት ካሉ እኩልነት ምን ማለት እንደሆነ ያልገባቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። በእነዚህ ወገኖች አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረ-ሰቦች ለጠ/ሚኒስተርነት ወረፋ ሊደለድልላቸው ይግባል ማለት ይመስለኛል። ይህ ካላዋቂነት የመጣ አስተሳሰብ ነው እንደ መሰለኝ።*

*ሁለተኛ ይህንን ስልጣን እንደ ጠበል ሁሉም ጋ መዳረስ አለበት ከሚሉት ወገኖች ተቃራኒ እና በእውነት የሁሉም ብሔር ብሔር-ሰቦችን እኩልነትን የሚጻረር እና የአንዱን ብሔር የበላይነት ከመመኘት የሚመነጭ ነው። ጤናማነት የጎደለው በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ግዜም የማይፈጸም ሕልም ነው።*

*ለመንግስት መሪነት ብቃት ያለው ከየትኛውም ብሔር መምጣት አለበት። ምናልባት በጥናት የተደገፈ እውቀት የለኝም እንደ ግምቴ ኩናማ አነስተኛ ህዝብ ያለበት ብሔረ-ሰብ ይመስለኛል። ስለዚህ ብቃት ካለው የኩናማ ተወላጅ ቢመጣ ከልብ አሜን ብለን መቀበል ይኖርብናል። ከኦሮሞም ብቃት ያለው ቢመጣ በደስታ መቀበል ይኖርብናል። መመዘኛችን ብቃትን እንጂ ምን ያህል የህዝብ ብዛት አለበት? የሚል መሆን የለበትም። ከዘረኛው ከጠባብተኝነት ከትምክሕት የጸዳን መሆን ይጠበቅብናል። አሳፋሪ፡ አስነዋሪ አስተሳሰብን መጠየፍ ይኖርብናል።*

ይህንን ያልሰለጠነው ኋላ ቀር አስተሳሰብ እና አመለካከት በተራ የሕብረተ-ሰብ ክፍል ብቻ ያለ አይደለም። በምሑሩ ክፍል፡ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በአንድ አንድ የአመራር አባላትም ይኖራል። በተለይ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ያሉ ሰዎች ይህንን አስተሳሰብ ይዘው እንዴት የድርጅቶቹ አማራር መሆን እንደቻሉ በጣም ይገርማል። ለምን ይህንን አስተሳሰብ እንዲኖራቸው በቁ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ይህንን አስተሳሰብ የሚያራምዱ ወገኖች፡ የስልጣን ርሐብ ያላቸው፡ በብቃት ተመዝነው ለመሪነት መድረስ ስለማይችሉ የኦሮሞን ህዝብ፡ የአማራን ህዝብ ምክንያት በማድረግ የስልጣን ኮረቻውን ለመቀመጥ ካላቸው ፍላጎት ብቻ ይመነጫል። እውነት ለኦሮሞ ህዝብ፡ ለአማራ ህዝብ በማሰባቸው ነው እንዲህ የሚሆኑት? መልሱ አይደለም ነው። በእውነት ለኦሮሞ ህዝብ ብያስቡ ኦሮምያ ላለፉት ሦስት አመታት ሰላምዋን ከመታወክ በታደጓት ነበር። በቅርቡ 800,000 ህዝብ ያፈናቀለውን ስንት ሂወት የቀሰፈውን ስንት ንብረት ያወደሞውን ረብሻ ከጅምሩ ባስቆሙት ነበር ለኦሮሞ ህዝብ ብያስቡና ብቆረቆሩ ኖሮ።

ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ እውነት ስለአገር የምንጨነቅ የምናስብ ከሆነ ኋላ-ቀር አስተሳሰቦን ከዘር ከጠባብተኝነት፡ ከትምክሕት የጸዳ አስተሳሰብ ልናዳብር ይገባል። ኢትዮጵያን የሚመራ ከየትኛውም ዘር ይሆን ልንቀበለው ይገባል። እንደየ አቅማችን ልንደግፈው ይገባል። ቢሳሳት ልንደግፈው ይገባል። መልካም ሥራአቹን ልንደግፍ ይገባል። መነጻራችን ዘርን ሳይሆን ብቃትን መሆን ይገባል።

# <u>ማጠቃለያ</u>

ኢህአዴግ ጠንካራ እና ብቁ በሥራ የተፈተነ መሪ ያስፈልገዋል። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ ጠንካራ ብቃት ያለውን መሪ ከምንም ግዜ በላይ ትሻለች። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ያንን ሰው መፍጠር አልቻሉም። በየድርጅቱ ተመጣጣኝ ብቃት ያላቸው ሊቀ-መናብርትን መፍጠር ተስኗቸዋል። አሳዛኝ ነው። ግን ምን ይደረግ ካሉት መሪዎች ግን የበለጠ ሰው የኢህአዴግ ሊቀ-መንበር መሆን የግድ ነው።

ሌላው አሳዛኝ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ኢህአዴግን መወዳደር የሚችል ሌላ ፖለቲካዊ ድርጅት አለመኖሩ ነው። ያሉን የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸውን አደራጅተው ብቃት ያለው አገርንን መምራት የሚችል ድርጅት መፍጠር አለመቻላቸውን ነው። ብቁ ድርጅት ፈጥረው ከኢህአዴግን ስልጣን ከመረከብ ይልቅ በኢህአዴግ ችሮታ ፓርላማ መግባት የሚፈልጉ ብቻ ናቸው። በህዝብ ሳይመረጡ ከፓርላማ 10% መቀመጫን እንዲሰጣቸው ኢህአዴግን የሚለምኑ ድርጅቶች ነው ያሉን። ይህ እውነት አለመታደል ነው። ኢህአዴግን የሚወዳደር አንድ ፖለቲካዊ ድርጅት ቢኖረን፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢህአዴግ ቢማረር ሌላ ድርጅት ስልጣኑን እንዲረከብ ማድረግ ይችል ነበር። ግን ሣይሰሩ መክበር በፓርላማ ወንበር የሚፈልጉ ድርጅቶች የበዙባት ሚስኪን አገር ሆናለች ኢትዮጵያ። ኢህአዴግ 10% የፓርላማ ወንበር በችሮታ ሰጥታቸዋል። በህዝብ ድምጽ ሊሰጥ የሚገባ ስልጣን ኢህአዴግ ወንበሮችን የመስጠት መብት ሊኖረው አይገባም ነበር።

ትልቁ የመንግስት ስልጣን ፓርላማን ነው። ይህ ስልጣን የሚሰጠው እና የሚነሳው ህዝብ እንጂ ኢህአዴግ አይደለም። ይህንን አካሔድ በእውነት ዲሞክራሲን ማስፋት ሳይሆን ዲሞክራሲን መጻረር ነው። ፖለቲካዊ ምህዳሩን እንዳይሰፋ ምክንያት እየሆኑ ያሉ እንደ እኔ እምነት ተቃዋሚ ተብየ ድርጅቶች ናቸው። የህዝብ ስልጣን ካለ አግባብ እንዲቸበቸብላቸው ኢህአዴግን እየለመኑ የሚገኙት። ስልጣን የሥራ ውጤት እንጂ በችሮታ የሚደለደል የሚሰጥ መሆን አልነበረበትም።

ከላይ ስለ አራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የእኔ አመለካከት ማስቀመጥ ሳስብ ስለ ሁሉም ድርጅቶች አወንታዊ ክንውኖች አልነካሁም። አወንታዊ ሥራዎቻቸውን አቅማቸውን ለማስገንዘብ የጽሑፌን መነሻ አልነበረም። ለዚህም ነው እዛ ላይ ያልገባሁት።

ኢትዮጵያ ይህንን ያለንበትን አዲሱ ሥርዓት ከተመሰረተ አንስቶ በሁሉም መስኮች በሚገርም መልኩ ተአምራዊ እድገት ሥታስመዘግብ ቆይታለች አሁንም እያስመዘገበች ነው። በየክልሉም ይሁን በአገር አቀፍ ደረጃ አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ

ናቸው። ይህንን መካድ የማይቻለው የሁሉም ድርጅቶች የሥራ ውጠት ነው። ችግሮች ቢኖሩም በተቻለ መጠን መፍትሔ እያገኙ ይገኛሉ።

አሁን እያጋጠሙን ያሉት ኢኮኖምያዊ ፡ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ከዚህ ቀደም ሥር የሰደዱ ስለነበሩ፡ አሁን ለሚፈጠሩ ችግሮቻችን የራሳቸው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም። በዚህ መሰረት ለሚፈጠሩ ሁሉም ዓይነት ፈተናዎች በሚፈለገው ደረጃ ባይሆንም እንኳን ኢህአዴግ እንደ ኢህአዴግ ከክልሎች እስከ አገር አቀፍ የቤት ሥራውን በመስራት ተመጣጣኝ መልካም ውጤቶች እያስመዘገበ ይገኛል።

እርግጥ ነው ኢህአዴግ ምሕረት የሌለው ጠንካራ ውስጠ ትግል ያስፈልገዋል። አሁን ላይ እየተከሰቱ ያሉት የጤና መጓደል በግዜው መታረምን ካልተቻሉ ለወደፊቱ ጠጥረው ኢትዮጵያን አደጋ ውስጥ ይጥሏታል። ስለዚህ በኢህአዴግም ሆነ በአባል ድርጅቶች እውነተኛ ህዝባዊነት የተላበሰ ትግል የግድ ይላል።

በመጨረሻ ኢህአዴግ አጋር ድርጅቶች የሚላቸውን ድርጅቶች በአባል ድርጅቶች የሚተኩበት ማእቀፍ ቢፈጥር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። ኢህአዴግ በአራቱ ክልሎች መውወሰኑን ተሻግሮ ሁሉም ክልሎች መዳረስ ያለበት ግዜ የደረሰን ይመስለኛል።

**ቸር እንሰንብት**

***ተጋዳላይ ነኝ***

03-27-18

alula.humermetkel@gmail.com